

# ስማ!

የምትሰማ    ስማ- አልያ ...ሂድ ተወው
ፉከራህ ጉራ ነው -እሳት ያልፈተነው::
        የዘር ፖለቲካ -የጥላቻ ዘር ነው
        ጥላቻን አብቅሎ- ጥላቻን ያፈራው::
ሁሉም ቢተባበር- አይኑ ሰላም ቢሻ...
አንድነትን ቢሻ
ሹልክ ባይል ከጎን-በእርስ በእርስ ረብሻ
አይናችን ያይ ነበር-መልካም መጨረሻ::
        የዘር ፖሊቲካ- ዘረኛ ነው ላይል-ራስ ወዳድ ሆኖ
        በጥላቻ ድር ውስጥ-ጋቢ አርጎ ጀቡኖ
        የትም አይደረስ
        እስከ ወዲያው ድረስ
ስማ!
ስማ!
ስማ እደግመዋለሁ!

        የበይወች አለመስማማት- ሲበጅ ለሚበላው
        የተበይወች መስማማት -በያቻውን በላው::

የካቲት 2007 ዓ.ም.
ድሬዳዋ ኢትዮጵያ